በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ
Addis Ababa City Administration Innovation and
Technology Development Bureau

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለስራ ሃላፊዎችና ፈፃሚዎች የሚውል ተንቀሳቃሽ ዋይፋይ አጠቃቀም መመሪያ

ጥቅምት 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መስሪያ ቤቶች ውስጥ ለስራ ሃላፊዎችና ፈፃሚዎች የሚውል ተንቀሳቃሽ ዋይፋይ ሥራን ማዕከል ያደረገ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ያከበረ መሆን እንዳለበት በመታመኑ፤

የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ አገልግሎት የሚያገኙ የሥራ ሃላፊዎች እና ፈፃሚ ባለሙያዎች ፈቃድ ስለሚያገኙበት እና የአጠቃቀም ሁኔታ ላይ ወጥ እና ግልፅ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ቢሮው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀጽ 2(ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1) **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ **"ለስራ ሃላፊዎችና ፈፃሚዎች የሚውል ተንቀሳቃሽ ዋይፋይ አጠቃቀም መመሪያ"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2) **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

1) **"ከተማ አስተዳደር"** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማለት ነው፡፡
2) **"ቢሮ"** የከተማ አስተዳደሩ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ማለት ነው፡፡
3) **"የስራ ሃላፊዎች"** በከተማ አስተዳደሩ የከተማ እና የክ/ከተማ የአስተዳደር እርከኖች በተለያዩ ቢሮዎች እና ጽ/ቤቶች ተሹመው በማገልገል ላይ ያሉ አመራሮች ማለት ነው፡፡
4) **"ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር"** በሴክተሮች ደረጃ ተደራጅተው ቴክኒካል ተግባራትን በበላይነት እየመሩ ያሉትን ማለት ነው፡፡
5) **"ተንቀሳቃሽ ዋይፋይ"** ከኢትዮቴሌኮም በገመድ አልባ መንገድ እየተሰጠ ያለው የኢንተርኔት አገልግሎት ማለት ነው፡፡
6) **"ፈፃሚ"** በከተማ አስተዳደሩ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሰራና ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪው ውስጥ የተጠቀሰ ማንኛውም ሰራተኛ ማለት ነው፡፡
7) **"ያለገደብ"** ኢትዮቴሌኮም በተወሰነ ክፍያ መጠን ያልተገደበ የኢንተርኔትና ዳታ አገልግሎት ለመስጠት ባወጣዉ የጥቅል አገልግሎት ክፍያ አሰራር መሰረት የሚፈጸም ማለት ነዉ፡፡
8) **"ገደብ"** ኢትዮቴሌኮም በተወሰነ ክፍያ መጠን የተገደበ የኢንተርኔትና ዳታ አገልግሎት ለመስጠት ባወጣዉ የጥቅል አገልግሎት ክፍያ አሰራር መሰረት የሚፈጸም ማለት ነዉ፡፡
9) **"ፓኬጅ"** ማለት ኢትዮቴሌኮም በሚሰጠው ጥቅል የኢንተርኔትና ዳታ አገልግሎት ተጠቃሚነት የሚሆንበትን አሰራር መሰረት የሚፈጸም ማለት ነዉ፡፡
10) **"የፆታ አገላለፅ"** በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴት ፆታን ይጨምራል፡፡

3) **ተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ተንቀሳቃሽ ዋይፋይ በተፈቀደላቸው የከተማ አስተዳደሩ የሥራ ሃላፊዎች እና ፈፃሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

4) **ዓላማ**

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት

1) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለስራ ሃላፊዎችና ፈፃሚዎች የሚውል ተንቀሳቃሽ ዋይፋይ አጠቃቀም ሥራን ማዕከል ያደረገ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ያከበረ እንዲሆን ማድረግ፤ እና
2) ተንቀሳቃሽ ዋይፋይ የሚያገኙ የሥራ ሃላፊዎች እና ፈፃሚ ባለሙያዎች ፈቃድ ስለሚያገኙበት እና አጠቃቀም ሁኔታ ወጥ እና ግልፅ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት።

# ክፍል ሁለት

## ስለ አገልግሎት ፈቃድ፣ በጀት እና ክፍያ አፈፃፀም

### 5) ስለ አገልግሎት ፈቃድ

1) ተንቀሳቃሽ ዋይፋይ የሚያገኙት በዚህ መመሪያ አባሪ አንድ የተፈቀደላቸው ሃላፊዎች እና ፈፃሚዎች ናቸው፡፡

2) በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቢሮው ኦፕሬሽንና አገልግሎት ዘርፍ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሚከተሉት ምክንያቶች የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል፡-

   ሀ) ከስራ ባህሪያቸዉ አንፃር ወይም በአዲስ መልኩ ከሚፈጠር አደረጃጀት ጋር በተያያዘ ጥያቄ መስሪያ ቤቶች ሲያቀርቡ፤ ወይም

   ለ) በአባሪ አንድ ከተፈቀደላቸው የስራ መደቦች በተጨማሪ ለቢሮው፣ ለክፍለ ከተማ እና ወረዳ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ጽሕፈት ቤት ለሚሰሩ ባለሙያዎች ከስራ ባህሪያቸዉ አንጻር የኢንተርኔትና የዳታ አገልግሎት ጥያቄ ሲቀርብ ነው፡፡

### 6) በጀት

ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ለኢንተርኔት እና ዳታ መስመር አገልግሎት ክፍያ የሚዉል በጀት በሚመደበው መሰረት በመስሪያ ቤቶች የበጀት አርዕስት ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በሚውል (consolidate account) ስር ይያዛል፡፡

### 7) ክፍያ አፈፃፀም

1) ወርሃዊ የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ ክፍያ በዚህ መመሪያ አባሪ አንድ በተቀመጠው የክፍያ ጣሪያ መሰረት ይፈፀማል፡፡

2) በገደብ ተብሎ ለተፈቀደው የገመድ አልባ ዋይፋይ ክፍያ ከኢትዮቴሌኮም ጋር ስምምነት ላይ በመድረስ የቅድመ ክፍያ (prepaid) አገልግሎት መሆን አለበት፡፡

3) ከተፈቀደው የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ ታሪፍ በላይ የተጠቀመ በክፍያው ደረሰኝ መሰረት ልዩነቱን እንዲሸፍን ይደረጋል፡፡

4) ያለ በቂ ምክንያት ከሶስት ጊዜ በላይ ከታሪፍ በላይ የተጠቀመ እና ከታሪፍ በላይ የተጠቀመውን ክፍያ ያልከፈለ ማንኛውም የስራ ኃላፊ ፣ ዳይሬክተርና

ባለሙያ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት በዲሲፕሊን ይጠየቃል፡፡

5) በንዑስ አንቀጽ 4 ሥር የተደነገገዉን ተፈፃሚ ለማድረግ በቅድሚያ ከኢትዮ ቴሌኮም የኢንተርኔት ፍጆታ ክፍያ ደረሰኝ ለተጠቃሚው እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡

6) የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ ክፍያ የሚፈፀመው ኢትዮቴሌኮም የሚልከውን የሂሳብ ደረሰኝ በማመሳከር ሲሆን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች መጠበቃቸዉን የኦፕሬሽንና አገልግሎት ዘርፍ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

7) ቢሮው በከተማ አስተዳደሩ ስር በሚገኙ መስሪያ ቤቶች ለሚሰሩ ስራዎች አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከተቀመጠው የክፍያ ጣሪያ በላይ በልዩ ሁኔታ ጥያቄ ሲቀርብለት ሊፈቅድ ይችላል፡፡

8) በንዑስ አንቀጽ 7 ሥር በተደነገገዉ መሰረት የሚቀርበው ጥያቄ ተግባራዊ የሚደረገው ከተቀመጠው የክፍያ ጣሪያ በላይ በአማካይ በወር ምን ያህል ፍጆታ እንደሚያስፈልግ በጽሁፍ ከዝርዝር ማስረጃዎች ጋር ለቢሮው ጥያቄ ሲቀርብ ቢሮውም የቀረበውን ጥያቄ ከመረመረ በኂላ አገልግሎቱን በሚመራው ዘርፍ ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## 8) ስለ አስፈፃሚ አካላት ተግባርና ሃላፊነት

1) **ቢሮው** የመመሪያውን አጠቃላይ አፈጻጸም የመከታተል እና ችግሮችም ሲኖሩ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡፡

2) **የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ኦፕሬሽንና አገልግሎት ዘርፍ፡-**

   ሀ) በዚህ መመሪያ መሰረት ለሃላፊዎችና ፈፃሚዎች የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ ጥያቄ ይቀበላል፣ አስፈላጊነቱን ሲያምንበት ይፈቅዳል፤

   ለ) ከኢትዮ-ቴሌኮም ጋር በመሆን በተፈቀደዉ አግባብ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ ማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የስማርት ሲቲ ዘርፍ የዚህን መመሪያ ተፈጻሚነት በበላይነት የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡

4) **በክፍለ ከተማ እና ወረዳ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ጽሕፈት ቤትና ተቋማት፡-**

   ሀ) የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ የተፈቀደላቸው የስራ ሃላፊዎችና ፈፃሚዎች በተለያዩ ምክንያቶች መስሪያ ቤቱን ሲለቁ ወይም ለረጅም ግዜ በስራ ላይ በማይገኙበት ግዜ

የተፈቀደውን የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ መመለሳቸውን መቆጣጠር፡፡

ለ) ከተጠቃሚዎች ለሚቀርቡ የድጋፍ ጥያቄዎች አስፈላጊውን ምላሽ መስጠትና ከአቅም በላይ የሆነ ጥያቄ ሲቀርብ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ኦፐሬሽንና አገልግሎት ዘርፍ ማሳወቅ፡፡

# ክፍል ሦስት

## ስለ አጠቃቀም፣ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት

### 9) ተቀባይነት ስላለው አጠቃቀም

1) በዚህ መመሪያ መሰረት የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም ሃላፊ እና ፈፃሚ በሃላፊነት፣ በሥነ-ምግባራዊ እና በሙያዊ አኳኋን ለሕጋዊ የሥራ ዓላማ እንዲጠቀም ይጠበቅበታል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ መጠቀም የሚችለው የሚከተሉትን ተቀባይነት ያላቸውን ተግባራት ለመፈፀም ይሆናል፡-
    ሀ) ከስራ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን እና መተግበሪያዎችን ለማውረድ፤
    ለ) ከሥራ ባልደረቦች፣ ተገልጋዮች እና ባለድርሻ አካላት ጋር ለሥራ ዓላማ ግንኙነት ለመፍጠር፤
    ሐ) ከሥራ ተግባራት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ምርምር እና ጥናት ለማካሄድ፣ እና
    መ) ከሙያ ጋር የተገናኙ የማህበራት የውይይት መድረኮች ውስጥ ለመሳተፍ ፡፡
3) ተጠቃሚዎች የተፈቀደላቸውን የአገልግሎት እና ሴሪያል ቁጥር ማስመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡

### 10) የተከለከሉ ተግባራት

ማንኛውም ሰው የተንቀሳቃሽ ዋይፋይ በሚጠቀምበት ወቅት የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም በጥብቅ የተከለከሉ ናቸው፡-

1) ለስራ የተፈቀደውን የዋይፋይ ቀፎና ሲምካርድ ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት፤
2) አገልግሎት የሚጠቀም አመራርም ሆነ ፈፃሚ ከስራ ኃላፊነቱ ወይም ተቀጥሮ ከሚሰራበት መስሪያ ቤት ሲለቅ፣ ሲዘዋወር ወይም ለረጅም ጊዜ ትምህርት እና ስልጠና በመስሪያ ቤቱ ከሌለ ተመላሽ አለማድረግ፤
3) ያለፍቃድ የሌላ ሰው ኮድ ወይም ይለፍ ቃል መጠቀም፤

4) የአፀያፊ፣ የትንኮሳ፣ የአድሎአዊ ወይም የማስፈራሪያ ይዘት ያላቸውን ፅሁፎች፣ ምስሎች፣ ተንቀሳቃሽ ቪድዮ ማጋራት ወይም ማውረድ

5) በቁማር፣ በኦንላይን ጌም ወይም ከሥራ ጋር ባልተያያዙ የግል ግብይቶች መሳተፍ፤

6) የመስሪያ ቤቱን የስራ ሚስጥራዊ መረጃን ማጋራት፤

7) ያልተፈቀደ ሶፍትዌር መጫን ወይም ያልተፈቀዱ ድረ-ገጾችን መጎብኘት፤

8) የአዕምሮአዊ ንብረት መብቶችን መጣስ ወይም በሳይበር ወንጀል ተግባራት ውስጥ መሳተፍ፤

9) የፍቃድ ስምምነቶችን ማክበር አለመቻል፤ እና

10) የመስሪያ ቤቱን የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴዎች ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ።

## 11) ቁጥጥር እና ምርመራ

ቢሮው ተጠቃሚው ከዚህ የአጠቃቀም መመሪያና ስርዓት በተቃራኒ ተንቀሳቅሷል የሚል ምክንያታዊ የሆነ ጥርጣሬና ግምት ሲኖረው ወይም የመስሪያ ቤቶችን ደህንነት ለመጠበቅ የሲስተም ሎግ ኦዲት የማድረግ ወይም የበይነመረብ አጠቃቀምን የመቆጣጠር መብቱ የተጠበቀ ነው።

## 12) ብልሽት የማሳወቅ ሃላፊነት

1) ማንኛውም ተጠቃሚ እገዛ የሚያስፈልገው ቴክኒካዊ ችግር ሲገጥመው በየተቋማቱ ላሉት የኦፐሬሽንና ጥገና ክፍል በደብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢ-ሜይል ማሳወቅ አለበት።

2) የኦፐሬሽን ጥገና ክፍል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ጥያቄ ሲቀርብለት በተቻለ ፍጥነት የተጠየቀውን እገዛ፣ ድጋፍ ወይም ጥገና የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

## ክፍል አራት

## ልዩ ድንጋጌዎች

13) **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም የከተማ አስተዳደሩ የመስሪያ ቤት ሃላፊ እና ፈፃሚ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

14) **ተጠያቂነት**

ማንኛውም ተጠቃሚ ከዚህ መመሪያ፣ አግባብነት ካላቸዉ ሌሎች የቢሮው የኢንተርኔት አጠቃቀም መመሪያ፣ ስርዓት፣ ስታንዳርዶች እና መርሆዎች በተቃራኒ ከተጠቀመና ይህንኑ በተጨባጭ ማስረጃ ማረጋገጥ ከተቻለ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

15) **ተፈፃሚነት የሌላቸዉ ህጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ አስተዳደራዊ ውሳኔ እና ልማዳዊ አሠራር ተፈፃሚነት የለውም፡፡

16) **መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በቢሮው ከፀደቀበት ከ ----------- ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሰሎሞን አማረ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ

15. አባሪ 1

| ተ.ቁ | የተፈቀደለት የኃላፊነት እርከን /መጠሪያ | የተፈቀደለት መጠን | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ከንቲባ | ያለገደብ | 5G |
| 2 | ም/ከንቲባ | ያለገደብ | 5G |
| 3 | በም/ከንቲባ ደረጃ የተሾሙ ኃላፊዎች | ያለገደብ | 5G |
| 4 | አፈ-ጉባኤ | ያለገደብ | 5G |
| 5 | ም/አፈ-ጉባኤ | ያለገደብ | 5G |
| 6 | በካቢኔ ደረጃ የተሾሙ ኃላፊዎች | ያለገደብ | 5G |
| 7 | በከንቲባ ሹመት ያገኙ የቢሮ ኃላፊዎች | ያለገደብ | 5G |
| 8 | በከንቲባ ሹመት ያገኙ የኤጀንሲ መስሪያ ቤት ኃላፊዎች | ያለገደብ | 5G |
| 9 | በከንቲባ ሹመት ያገኙ የባለስልጣን መስሪያ ቤት ኃላፊዎች | ያለገደብ | 5G |
| 10 | በከንቲባ ሹመት ያገኙ የኮሚሽን መስሪያ ቤት ኃላፊዎች | ያለገደብ | 5G |
| 11 | ምክትል ቢሮ ኃላፊዎችና በም/ቢሮ ኃላፊ ደረጃ የተሾሙ ሃላፊዎች | ያለገደብ | 5G |
| 12 | የኤጀንሲ ምክትሎች፤ በባለስልጣን መስሪያ ቤት ምክትሎች ፤ምክትል ኮሚሽነሮችና በምክትል ደረጃ የተመደቡ አማካሪዎች፤ | ያለገደብ | 4G |
| 13 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ዳይሬክተሮችና በዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ደረጃ ላሉ ቴክኒካል አማካሪዎች | ያለገደብ | 4G |
| 14 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የዳታ ሴንተርና ክላውድ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች | ያለገደብ | 4G |
| 15 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የኢኖቬሽን ጥናትና ምርምር ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች | ያለገደብ | 4G |

| ተ.ቁ | የተፈቀደለት የኃላፊነት እርከን /መጠሪያ | የተፈቀደለት መጠን | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 16 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ አቅም ግንባታና ስልጠና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች | ያለገደብ | 4G |
| 17 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የመሰረተ ልማትና ዲዛይን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች | ያለገደብ | 4G |
| 18 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ፕሮጀክት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች | ያለገደብ | 4G |
| 19 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የኢንፎርሜሽን ሲስተም ደህንነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች | ያለገደብ | 4G |
| 20 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የሶፍትዌርና ፕላትፎርም ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች | ያለገደብ | 4G |
| 21 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኦፕሬሽንና ጥገና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ ቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች | ያለገደብ | 4G |
| 22 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ደጋፊ የስራ ሂደት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮችና ቡድን መሪዎች | ያለገደብ | 4G |
| 23 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ስር ባሉት አንዳንድ ደጋፊ የስራ ሂደቶች ውስጥ ላሉት ሠራተኞች እንደ ስራ ባህሪያቸው ታይቶ በኦፕሬሽንና አገልግሎት ዘርፍ የሚፈቀድ | በገደብ | 4G |
| 24 | በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ በዳይሬክተር ደረጃ ላሉ ቴክኒካል አማካሪዎች | ያለገደብ | 4G |
| 25 | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ባሉ ሴክተር ቢሮዎች ያሉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮች | ያለገደብ | 4G |
| 26 | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ባሉ ኤጀንሲ መስሪያ ቤቶች ያሉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮች | በገደብ | 4G |
| 27 | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ባሉ ባለስልጣን መስሪያ ቤቶች ያሉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮች | በገደብ | 4G |

| ተ.ቁ | የተፈቀደለት የኃላፊነት እርከን /መጠሪያ | የተፈቀደለት መጠን | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 28 | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ባሉ ኮሚሽን መስሪያ ቤቶች ያሉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተሮች | በገደብ | 4G |
| 29 | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ባሉ ቢሮዎች አንዳንድ የስራ ዘርፎች እንደ ስራ ባህሪያቸዉ አሳማኝ ምክንያቶች ለቢሮው ቀርበዉ በመስሪያ ቤቱ በሚመለከተው ዘርፍ ኃላፊ የሚፈቀድ | ያለገደብ/በገደብ | 4G |
| 30 | የክ/ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚዎችና የህዝብ ግንኙነት አማካሪዎች | ያለገደብ | 4G |
| 31 | የክፍለ ከተማ ፅ/ቤት ሃላፊዎችና የዋና ስራ አስፈፃሚ አማካሪዎች | በገደብ | 4G |
| 32 | የክፍለ ከተማ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ጽ/ቤት አስተባባሪዎች | ያለገደብ | 4G |
| 33 | በክፍለ ከተማ ስር የሚገኙ አንዳንድ የስራ ዘርፎች እንደ ስራ ባህሪያቸዉ አሳማኝ ምክንያቶች ለቢሮው ቀርበዉ በኦፕሬሽንና አገልግሎት ዘርፍ ኃላፊ የሚፈቀድ | በገደብ | 4G |
| 34 | የወረዳ የዋና ስራ አስፈፃሚ | ያለገደብ | 4G |
| 35 | የወረዳ ኮሚዩኒኬሽን ዘርፍ ሃላፊዎች | በቴሌ ፓኬጅ | |
| 36 | የወረዳ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቡድን መሪዎች | በገደብ | 4G |
| 37 | በወረዳ ስር የሚገኙ አንዳንድ የስራ ዘርፎች እንደ ስራ ባህሪያቸዉ አሳማኝ ምክንያቶች ለቢሮው ቀርበዉ በኦፕሬሽንና አገልግሎት ዘርፍ ኃላፊ የሚፈቀድ | በገደብ | 4G |

**በገደብ የተፈቀደላቸው መጠን /መጠሪያ**

| ተ.ቁ | የተቀደለት የኃላፊነት እርከን /መጠሪያ | የተፈቀደለት መጠን | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | በገደብ የተፈቀደላቸው ወርሀዊ መጠን እስከ 600 ብር ይሆናል | 600 ብር | |